በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሐገረ ስብከት ጽ/ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahdo Church Diocese of Northern California, Nevada, and Arizona Main Office

ነሐሴ ፳፰ ፳፻፲፬ ዓ/ም
ሰካሀጽ 93I22

"ወሠናየ ሐልዩ ለቅድመ እግዚአብሔር ወለቅድመ ሰብእ"
"ለሰውም ለእግዚአብሔርም መልካሙን ነገር አስቡ" ፪ኛቆሮ ፰÷፳፩

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን**

**ከነሐሴ ፳፯ እስከ ነሐሴ ፳፰ ፳፻፲፬ ዓ/ም / Sept 2 & 3 2022 በደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላስ ቬጋስ የተካሄደው የሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ፪ተኛው የካህናት ፣ ሰበካ ጉባዔ እና ሰንበት ት/ቤት አጠቃላይ ስብሰባ መግለጫ፤**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰሜን ካሊፎርኒያ ፣ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ለሁለተኛ ጊዜ የተካሄደው የሀገረ ስብከቱ አጠቃላይ ስብሰባ ብጹዕ አቡነ ቴዎፍልስ ዶ/ር የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ፣ ቆሞስ መልአከ ስብኃት አባ ኃ/ኢየሱስ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፣ በሀገረ ስብከቱ የሦስቱም ወረዳ ቤ/ክህነት ኃላፊዎች ፣ የመምሪያ ኃሊፊዎች ፣ እንዲሁም በሀገረ ስብከቱ ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባዔ እና የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች በተገኙበት ነሐሴ ፳፯ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም በይፋ ተጀምሮ በአጀንዳ በተያዙ እና በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ጉባዔው ውይይት ሲያደርግ ከቆየ በኋላ ለአጥቢያው አብያተ ክርስትያናት እንዲሁም ለሀገረ ስብከቱ በሚጠቅሙ ጉዳዮች ውሳኔ በማሳለፍ ስብሰባው ነሐሴ ፳፰ ቀን ፳፻፲፬ ዓ/ም ተጠናቋል።

ለስብሰባው መሳካት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት የተደረገ ሲሆን በሀገረ ስብከቱ አማካኝነት ለተቀረጹ አራት አጀንዳዎች በጥናታዊ ጽሁፍ መልክ ዘመኑን በዋጀ ምልኩ ለጉዳዩ በተመረጡ አካላት አማካይነት የዳሰሳ ጥናት ጽሁፍ ቀርቦ ጉባዔውም በቀረቡት ኃሳቦች በጥልቀት ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል።

በዚህም መሠረት ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቦ ውይይት የተደረገባቸው አጀንዳዎች፤

1. የክህነት አገልግሎት
2. መንፈሳዊ አገልግሎት እና የቤ/ክርስቲያ አስተዳደር
3. ትኩረት ለቤ/ክርስቲያ ተተኪ ትውልድ፤
4. የሀገረ ስብከቱ ራእይ እና አጠቃላይ መዋቅራዊ ዳሰሳ

በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አወያይነት የተመራው እና ለሁለት ቀናት በዘለቀው በዚህ ስብሰባ አጀንዳዎቹ በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የተስተናገዱ ሲሆን በጉባዔው መክፈቻ እለት የሀገረ ስብከቱ ልዩ ልዩ መምሪያዎች እና ወረዳ ቤ/ክህነት ኃላፊዎች አማካይነት የ፳፻፲፬ ዓ/ም የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት እና የ፳፻፲፭ ዓ/ም የሥራ እቅድ ቀርቧል።

በዚህም መሠረት ጥናታዊ ጽሁፎቹን እና ሪፖርቶቹን ለማቅረብ የሚመለከታቸው አካላት ላሳዩት ቀናነት እና ላደረጉት ልዩ ልዩ ጥረቶች ከብጹእነታቸው ምሥጋና ቀርቧል። በቀረቡ አጀንዳዎች እና የመወያያ ነጥቦችም ለስብሰባው በተሰየሙ የቃለ ጉባዔ አርቃቂዎች አማካይነት ቃለ ጉባዔ የተያዘ ሲሆን በስብሰባው ማጠናቀቂያ እለት ስለ ጉባዔው የውሳኔ ነጥቦች እና አጠቃላይ የስብሰባ ሂደት መግለጫ እንዲሰጥ እንዲሁም የመግለጫው ሙሉ ይዘት በሀገረ ስብከቱ የደብዳቤ ፕሮቶኮል ለቅጥቢያው አድባራት በአድራሻ እንዲላክ ውሳኔ ተሰጥቷል።

በስብሰባው ሂደት ውይይት ተደርጎ የጋራ ውሳኔ ለሚሠጥባቸው ጉዳዮችም ለተፈጻሚነታቸው የሀገረ ስብከቱ ክትትል ሚና እንዳለው በስብሰባው መጀመሪያ የተጠቆመ ሲሆን በስብሰባው የተገኙ የአጥቢያ ካህናት እና የሰበካ ጉባዔ ተጠሪዎች ፣ የሰንበት ት/ቤት አባላት እንዲሁም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ቴዎፍልስ ዶ/ር መመሪያ ተሰጥቷል።

**ውሳኔ፤**

**1. የክህነት አገልግሎት**

በክህነት አገልግሎት ዙርያ በሀገረ ስብከቱ የካህናት አገልግሎት መምሪያ አማካይነት ሰፊ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን በልዩ ልዩ ምክንያት ለሚከሰቱ የአገልግሎት እና የአገልጋይ ተግዳሮቶች ሁሉም ካህናት የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ ጉባዔው ወስኗል። ተግዳሮቶቹን በዘላቂነት ለመቅረፍም የካህናት አገልግሎት ስልጠና ዘመኑን በዋጀ መልኩ በሀገረ ስብከቱ መዋቅር መሠረት እንዲጀመር ጉባዔው ወስኗል። ስልጠናውን በመዋቅራዊ ይዘት ለማስጀመር ይረዳ ዘንድ የስልጠና ማእከል እና የስልጠናውን አጠቃላይ ይዘት እንዲቀረጽ ጉባዔው ውሳኔ አሳልፏል። በዚህም መሠረት ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት በሀገረ ስብከቱ የት/ት ማሰልጠኛ መምሪያ እና ልዩ ኮሚቴ አማካይነት ጥናቱ ተዘጋጅቶ ለሀገረስብከቱ እንዲቀርብ መመሪያ ተሰጥቷል።

**2. መንፈሳዊ አገልግሎት እና የቤ/ክርስቲያ አስተዳደር**

በመንፈሳዊ አገልግሎት እና የቤ/ክርስቲያ አስተዳደር አጀንዳ ዙርያ በኔቫዳ ወረዳ ቤ/ክህነት አማካይነት ሰፊ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን በቀረበው የጥናታዊ ጽሁፍ ኃሳብ ዙርያ ጉባዔው በሰፊው ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል። በዚህም መሠረት፤

- መንፈሳዊ አገልግሎት እና የቤ/ክርስቲያን አስተዳደርን ለማጣጣም በሚደረጉ ጥረቶች ምክንያት የሚከሰቱ ተግዳሮቶች በአገልጋዮች የኑሮ ሁኔታ እና በአጠቃላይ የቤ/ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ክፍተት እንዳይፈጥሩና የአገልግሎት መበደል ሁኔታ እንዳይፈጠር ጉባዔው በጋራ የወሰነ በዝርዝር ጉዳዮቹ ዙሪያ ካህናት በየአጥቢያቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በውይይት እንዲያዳብሩት ጉባዔው ወስኗል።

- መንፈሳዊ አገልግሎት እና የቤ/ክርስቲያን አስተዳደርን ለማጣጣም በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ጸድቆ በጥቅምት 2015 የሚመጣው ህገ ቤተ ክርስቲያን የካህናትን መብትና ግዴታ እንዲሁም በዚህ አጀንዳ በተነሱ ኃሳቦች ዙሪያ መልስ ለመስጠት አጠቃላይ መርሆችን ያካተተ ስለሚሆን መመሪያው ሲመጣ ለተፈጻሚነቱ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ውሳኔ ተሰጥቷል።

- በመቀጠል በመንፈሳዊ አገልግሎት እና የቤ/ክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳይ ዙርያ አሁን ላይ ለሚታዩ ጠንካራ ጎኖች ሁሉም ባለድርሻ አካል እንዲበረታ በብጹእነታቸው ምስጋና ቀርቧል። በአንጻሩም አልፎ አልፎ ለሚታዩ አስተዳደራዊ እና የአገልግሎት ተግዳሮቶች መስተካከል ካህናት እና የሰበካ ጉባዔ አስተዳደር አባላት በግድ ሳይሆን በውድ በጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ መመሪያ ተላልፏል።

- በተያያዥ ሀገረ ስብከቱ ለአጥቢያዎች መንፈሳዊ አገልግሎት መጠንከር የሚጠበቅበትን ለመፈጸም እና ለማስፈጸም ሦስቱም የወረዳ ቤ/ክህነት ጽ/ቤቶች በዋናነት እና በቅርበት እንዲሰሩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

በተጨማሪም ሀገረ ስብከቱን እና የኖኅተ ሰማይ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሃንስ ውቅድስት አርሴማ ገዳም ለማጠናከር ጉባዔው የመከረ ሲሆን የገቢ ምንጮችን በማሰናሰል ለሚደረገው ጥረት ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲወጣ መመሪያ ውሳኔ ተሰጥቷል። በዚህም መሠረት

- ለሀገረ ስብከቱ የሚደረግ ወርኃዊ የገንዘብ መዋጮ ክፍያን ሁሉም የሀገረ ስብከቱ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በተገቢው ጊዜ ገቢ እንያደርጉ ውሳኔ ተሰጥቷል።

- ለሀገረ ስብከቱ በየወሩ ከሚደረጉ የገንዘብ መዋጮዎች በተጨማሪ በሦስቱም ወረዳ ቤ/ክህነት እና በስራቸው በሚቋቋም አስተባባሪ ኮሚቴ አማካይነት በአመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ለሀገረ ስብከቱ እና በሥሩ ላለው ገዳም ማጠናከርያ የገንዘብ ማሰባሰቢያ መርሃግብር እንዲዘጋጅ ተወስኗል።

- በመጪው የ2015 ዓ/ም የመስቀል ደመራ እና ጥምቀት በዓላት በሦስቱም የወረዳ ቤተ ክህነቶች አስተባባሪነት በሚመለከታቸው አካባቢ ለሀገረ ስብከቱ የገቢ ማሰባሰቢያ መርኃግብር ተቀርጾ ሥራ እንዲሰራ እና አድባራትም ለተፈጻሚነቱ በትጋት እንዲሰሩ

- ከመንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የድጋፍ ገንዘብ የሚሰባሰብበትን መንገድ መረጃው እና እውቀቱ ያላቸው ምእመናን እንዲሁም ካህናት ተሳትፈው ጥናት ያለው ሥራ እንዲሰሩ ጉባዔው ወስኗል። ለተፈጻሚነቱም የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ክትትል የሚያደርግ ይሆናል።

**3. ትኩረት ለቤ/ክርስቲያ ተተኪ ትውልድ፤**

ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ ትውልድ ስለማፍራት በሚለው ጥናታዊ ጽሁፍ በሀገረ ስብከቱ ምክትል ጸሀፊ አማካይነት ሰፊ የዳሰሳ ጥናት የቀረበ ሲሆን በቀረበው ሰፊ እና ጠቃሚ የዳሰሳ ጥናት ጉባዔው በጥልቀት ከተወያየ በኋላ የመፍትሄ ኃሳብ ቀርቦ ውሳኔ አሳልፏል። በዚህም መሠረት፤

- በዳሰሳ ጥናቱ የቀረቡት ኃሳቦች ትውልድን ከመቅረጽ እና ከእቅበተ እምነት አንጻር ጠቃሚነታቸው የጎላ በመሆኑ በዋናነት ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ፣ ወላጆች እና አጠቃላይ ምእመናን የበኩላቸውን አስተዋጸኦ ያደርጉ ዘንድ ምክረ ኃሳብ ተሰጥቷል።

- ውጤት የሚያመጡ ስልታዊ እቅዶች ዝርዝር የያዘ መመሪያ በጥናት በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃ ተዘጋጅቶ በሀገረ ስብከት በኩል ሥራ ላይ እንዲውል ምክረ ኃሳብ ተሰጥቷል።

- የጉዳዩ ወሰን ሰፊ በመሆኑ ምክንያት ተጨማሪ ምክረ ኃሳብ እና የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያስፈልገው በመሆኑ መላው የሀገረ ስብከቱ አጥቢያ አገልጋዮች እና የአስተዳደር አባላት ከሀገረ ስብከቱ መመሪያ እስኪተላለፍ ድረስ ወቅታዊ ውይይት እያደረጉ አፋጣኝ የመፍትሄ አካላት እንዲሆኑ ጉባዔው ወስኗል።

- ሆኖም ግን ሀገረ ስብከቱ ለቤ/ክርስቲያን ተተኪ ትውልድ ወጥ የሆነ የአስተምህሮ መመሪያ እንደሚፈጥር የተገለጸ ሲሆን የአስተምህሮ መመሪያውን በዋናነት የሀገረ ስብከቱ የወጣቶች እና አገልግሎት ክፍል እንዲሁም የሰንበት ት/ቤት ማደራጃ መምሪያ ለዚህ ጉዳይ ከተሰየመ ኮሚቴ ጋር በጣምራ በመስራት መመሪያው እንዲዘጋጅ ጉባዔው ወስኗል።

**4. የሀገረ ስብከቱ ራእይ እና አጠቃላይ መዋቅራዊ ዳሰሳ በተመለከተ**

የሀገረ ስብከቱን ራእይ እና አጠቃላይ መዋቅራዊ ዳሰሳ በተመለከተ አስተዳደራዊ እውቀት እና ሙያ ባላቸው አገልጋዮች አማካይነት የዳሰሳ ጥናት የቀረበ ሲሆን ዳሰሳው በብዙ አቅጣጫ ሀገረ ስብከቱን ፣ አጥቢያዎችን እና የቅዱስ ሲኖዶስን ግንኙነት ባማከለ መልኩ የተዘጋጀ እንደሆነ ጉባዔው ከጥናቱ አቀራረብ ለመረዳት ችሏል። በዚህም መሠረት ለሀገረ ስብከቱም ሆነ ለአጥቢያዎች ሁለንተናዊ ሥጋቶች ጠንካራ ጎኖች ፣ ደካማ ጎኖች እና ምቹ አጋጣሚዎች ያሉ መሆናቸውን ዳሰሳው በስፋት አሳይቷል።

- በመሆኑም ጉዳዩ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተጨማሪ የውይይት መድረክ እንዲዘጋጅለት የተጠየቀ ሲሆን በቅድሚያ ግን የዳሰሳ ጥናቱ ለሀገረ ስብከቱ በጽሁፍ መልክ እንዲገባ ተወሰኗል።
- በመቀጠል በጽሁፍ ከሚቀርበው ጥናት ለአጥቢያዎችም ሆነ ለሀገረ ስብከቱ የሚጠቅሙ ሃሳቦች ላይ ጥልቅ ውይይት ተደርጎ በተጨማሪ ጥናት የመፍትሄ ሃሳብ እንዲቀርብ ጉባዔው ውሳኔ አሳልፏል።
- ለዚህም ጉባዔው በዋና አስፈጻሚነት የሀገረ ስብከቱን እቅድና ልማት መምሪያ እንዲሁም ልዩ ኮሚቴ በኃላፊነት ያስቀመጠ ሲሆን ጥናቱ እንደተጠናቀቀ የጥናቱ ውጤት ለሀገረ ስብከቱ ለውይይት እንዲቀርብ ወስኗል።

በመጨረሻም ይህን ጉባዔ የተሳካ ለማድረግ የተባበሩ የኔቫዳ ወረዳ ቤ/ክህነት ፣ የአጥቢያ አስተዳዳሪዎች ፣ ምእመናን እና መዘምራን ፣ የማህበረ ቅዱሳን ላስ ቬጋስ ንዑስ ማዕከል አባላት ፣ ጥናታዊ ጽሁፎቹን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማዘጋጀት ላቀረቡ አካላት ፣ እንዲሁም በጉባዔው ለመሳተፍ ከሩቅም ከቅርብም ለመጡ የሀገረ ስብከቱ የመምሪያ ኃላፊዎችና የወረዳ ቤ/ክህነት ኃላፊዎች ፣ የሰበካ ጉባዔ ተወካዮች እና የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነቴዎፍሎስ ዶ/ር ምሥጋና አቅርበዋል። ለተሰጡ መመሪያዎችና ለተላለፉ ውሳኔዎች ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽዖ በማድረግ ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ቆሞስ መልአከ ስብሃት አባ ኃ/ኢየሱስ የተጠናከረ መመሪያ ያስተላለፉ ሲሆን የ2015 ዓ/ም የሀገረ ስብከቱ ስብሰባ በኦክላንድ ካሊፎርኒያ እንዲሆን ጉባዔው በመወሠን በብጹእነታቸው ጸሎትና ቡራኬ ስብሰባው ተጠናቋል።